በቅድሚያ እቅድ ማውጣት፥ እራስዎን በደህንነት መጠበቅ

የቤት ውስጥ ግጭት/ሁከት ማስጠንቀቂያ ምልክቶችን ይወቁ እነዚህ ሁኔታዎች ይሻሻላሉ ወይም ምንም ሳይደረግ ይቆማሉ ብሎ መገመት አደገኛ ሊሆን ይችላል ብዙ ጊዜ ሁኔታዎቹ እየባሱ ነው የሚሄዱት።

የደህንነት ዕቅድ በማውጣት እርስዎና ልጆችዎ በአደጋ ጊዜ ምን ማድረግ እንደ አለባችሁ ታውቃላችሁ/ትዘጋጃላችሁ።

በዋሽንግተን ውስጥ የቤት ውስጥ ግጭት/ሁከት በሕግ የተከለከለ ነው ለምሳሌ ፕሮቴክሽን ኦርደር/ የፍርድ ቤት ማሳገጃ አግኝተው የሚጎዳዎን ሰው ከእርሶና ከልጆችዎ አጠገብ እንዳይደርስ ሊያደርጉ ይችላሉ።

በተጨማሪ ሀትላይንስ፤ መጠለያ፤ እና አድቮኬቶች/ደጋፊዎች መርዳት ይችላሉ

ከአጥቂዎ/ከሚጎዳዎ ሰው ውጪ እራስዎን ችለው ለመኖር የሚያስችሎትን የገንዘብ እርዳታ ሊያገኙ ይችላሉ።

የራስዎን ጉዳይ እራስዎ ይቆጣጠሩ፥ እርዳታ ለመጠየቅ አይፍሩ።

የቤት ውስጥ ግጭት/ሁከት ማስጠንቀቂያ ምልክቶች ምንድናቸው?

ባለቤትዎ ወይም የትዳር ጓደኛዎ፤

- በሕዝብ ፊት ይሰድብዎታል?
- የት እንደሄዱ፤ ከማን ጋር እንደተነጋገሩ ይመረምራል? ይቆጣጠራል?
- ጓደኞችንና ቤተሰቦችዎን ያንቋሽሻል?
- ቅናት የፍቅር ምልክት ነው ይላል?
- የተጎዱበትን ጉዳይ የእርሶ ጥፋት እነደሆነ ይነግሮታል?
- የት መሄድ እነደ አለቦት እና ምን ማድረግ እንዳለቦት ይወስናል?
- ገንዘብዎን ይቆጣጠራል?
- የግልዎ የሆኑትን ነገሮች ያጠፋል?
- እርስዎን፤ቤተሰብዎችዎን፤እቤት ውስጥ ያሎትን እንስሳት እጎዳለሁ እያለ ያስፈራራዎታል?
- በማይፈልጉበት ሰዓት ወይም በማይመችዎ ሁኔታ ግብረሥጋ ግንኙነት ያደርጋል?
- በሚያስፈራዎ ወይም በሚጎዳዎ ሁኔታ ይነካዎታል?
- ፍራቻዎ አላስፈላጊ ነው ይልዎታል?

ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት አንዱ እንኳን እርስዎ ላይ የሚፈጸም/የሚደርስ ከሆነ አደጋ ላይ ይሆናል ያሉት።

እርዳታ ከአድቮኬት በማግኘት የደህንነት ዕቅድ ያውጡ

የደህንነት ዕቅድ ወይም የደህንነት ዝግጅት ዝርዝር/ነጥብ

- በጉዳት/ጥቃት ሰዓት እንዴት ብለው ከቤት መውጣት እንዳለብዎት ያስቡ

- ከቤት መውጣት የማይችሉ ከሆነ እንዴት 911 መደወል እንደሚችሉ ያስቡ እርስዎ መደወል በማይችሉበት ወቅት ልጆችዎ እንዲደውሉ አስተምሩአቸው
- ለሚያምኑአቸው ጓደኞችዎ፤ ቤተሰብዎችዎ፤ እና ጎረቤቶች እቤት ውስጥ ስለ አለዎ ሁኔታ ይንገሩአቸው ለእርዳታ ሲጣሩ ከሰሙ ምን ማድረግ እንዳለባችው ያስጠኑአችው/ያስጠንቅቁአቸው
- የሚያጠቃዎ ሰው ከቤት ከወጣ በኃላ የቤትዎን በር ቁልፍና የስልክ ቁጥርዎን ይለውጡ ያጠቃዎትን ሰው በድንገት ቢያዩ/ቢያገኙ ወይም አጥቂው ተመልሶ መጥቶ እቤት ልግባ ቢልዎ ምን ማድረግ እንዳለቦት አስቡ/ዕቅድ ያውጡ
- እርስዎ ከቤት ከወጡ በደህንነት ሊያርፉበት የሚችሉበት ቦታ ያዘጋጁ የቤት ውስጥ ግጭት/ሁከት መጠለያ አንድ አማራጭ ሊሆንዎ ይችላል ያጠቃዎት ሰዎ የማያውቀው ቦታ ለመሄድ ቢመርጡ የበለጠ ነው
- አስፈላጊ የሆኑ ሰነድዎችዎን በሙሉ ኮፒ ያድርጉ የተለያየ ቦታ በቂ ኮፒዎች ያስቀምጡ ላድቮኬትዎና ለአንዳንድ ቤተሰብ አባላት ኮፒውን ይስጡ
- ሁልጊዜ በሚይዙት ቦርሳ ውስጥ እና ቶሎ ሊያዩት የሚችሉበት ቦታ ለድንገተኛ ግዜ የሚያስፈልጎትን የስልክ ቁጥር ዝርዝር ጽፈው ይያዙ/ያስቀምጡ እንደ 911 የሆኑ አስፈላጊ ቁጥሮችን በቃልዎ ያጥኑ
- በአደጋ ጊዜ ቶሎ ከቤት ለመውጣት ለእርስዎና ለልጆችዎ የሚሆን ልብስ፤መድሐኒት፤ አስፈላጊ ወረቀቶች እና ሌላ አስፈላጊ ነገር በቦርሳ አዘጋጅተው ደብቀው ቶሎ የሚያገኙት ቦታ ያስቀምጡ
- የፍርድ ቤት ማሳገጃ ለማውጣት ወይም ላለማውጣት ውሳኔ ለመድረስ ካቃቶት እና <u>ስለ ገንዘብ ምን ማድረግ</u> እንዳለቦት ካላወቁ ማለትም ይፍርድቤት ማሳገጃ ለመውጣት ገንዘበብ የሚያስፈለጎት ከሆነ አድቮኬትዎን ያማክሩ።

መውሰድ ያለቦት አስፈላጊ ነገሮች ዝርዝር ምሳሌ

- መታወቂያ ሰነዶች - የመንጃ ፈቃድ፣ ፓስፖርት፣ ግሪን ካርድ፣ የልደት ሠርተፊኬት፣ አይ-94፣ አይ - 20 የልጆች የልደት ሠርተፊኬት፤ የ ኢሚግሬሽን ሰነድ፤ ሶሻል ሰኪዩሪቲ ካርድ የሥራ ፈቃድ ካርድ
- የሕግ ሰነዶች - የፍርድቤት መሳገጃ፣ የጋብቻ ሠርተፊኬት፤ የኪራይ ውል፤ የመኪና ሊብሬ
- የገንዘብ ነክ ሰነዶች - የባንክ ሰቴትመንት፤ቼክ ደብተር፤የኤቲኤም ካርድ፤ ክሬዲት ካርድ፤ ታክስ ምላሽ
- ግንኙነት - አድራሻ መጻፊያ ማህደር፤ አስፈላጊ ስልከ ቁጥር ዝርዝር
- ዋጋ ያላቸው ነገሮች - ገንዘብ፤ጌጣጌጥ (ወርቅ)፤ ፎቶግራፍ፡ የልጆች አስፈላጊ መጫወቻ
- ቁልፍ - የቤት፤ የመኪና፤የቢሮ
- ጤና - መድሀኒት፤የክትባት ካርድ
- ስለ አጥቂው መረጃ - ሙሉ ስም፤ የትውልድ ቀን፤ ሶሻል ሰኪዩሪቲ ቁጥር፤ሕጋዊ ሁኔታ፤ የገቢ መረጃ፤በቅርብ ጊዜ የተነሱት ፎቶግራፍ

ያስታውሱ በቅድሚያ ሁኔታዎችን ካስተካከሉ/ከተጠነቀቁ ደህንነቶ የበለጠ ይሆናል።

ፕሮቴክሽን ኦርደር/የፍርድቤት ማሳገጃ

ጥቃት ከደረሰብዎ ፍርድቤት ሄደው መብትዎን ማስከበር ይችላሉ።

- ፕሮቴክሽን ኦርደር/የፍርድቤት ማሳገጃ ከቤት ውስጥ ግጭት/ሁከት የሚከላከል የፍርድቤት ትዕዛዝ ወረቀት ነው
- የዚህ አገር ተወለጅ ወይም ቋሚ ነዋሪም ባይሆኑ የፍርድቤት ማሳገጃ ማውጣት ይችላሉ እንዲያውም ይህ የትዕዛዝ ወረቀት የእርሶን ጥቃት ስለሚመዘግብ ለኢምግሬሽን ጉዳይዎ ይረዳዎታል
- የፍርድቤት ማሳገጃ አጥቂውን ሰው እነዳይገናኝዎ፤ እንዳያስፈራራዎ፤ እንዳይመታዎት፤ በወሲብ እንዳያጠቃዎ ፤ስልክ እነዳይደውልሎዎ ሊያዘው/ሊያደርገው ይችላል እንዲሁም ከቤት ውስጥ እንዲወጣ ሊያዘው ይችላል
- የፍርድቤቱን ትዕዛዝ የማያከብር አጥቂ ሊታሠር ይችላል ፤ለመታሠር ይፈረድበት ወይም ቅጣት እንዲከፍል ይሆናል አጥቂዎ የትዕዛዙን ማንኛውንም ነጥብ ከተላለፈ የግድ ለፖሊስ መደወል አለብዎ ወይም /በተጨማሪ ትዕዛዙን ያጸደቀው ፍርድቤት ተመልሶ በመሄድ ማሳወቅ አለቦት
- ሁልጊዜ የማሳገጃ ኮፒውን ይያዙት አጥቂው የማሳገጃ ትዕዛዙን ከተላለፈ/ከጣሰ ለፖሊስ የፍርድቤት ማሳገጃውን ያሳያሉ
- የፍርድቤት ማሳገጃ ኮፒውን ለልጆችዎ መዋዕለ ህፃናት፣ ትምህርት ቤት፡ ለሚያምኗችው ጓደኞችዎ፣ ለቤተሰብ አባሎች እንዲሁም የሚቻል ከሆነ ለአሠሪዎ ይስጡ
- የፍርድቤት ማሳገጃው/ትዕዛዙ ቋሚ አይደለም ካላሳደሱት ይቃጠላል
- ለጊዜው የልጆች ሞግዚትነት መብት ሊሰጦት ይችላል።

የተጠቁ ሴቶች መጠለያ እና ሕግ ደጋፊ ፕሮግራሞች ስለ ፕሮቴክሽን ኦርደር/የፍርድ ቤት መሳገጃ እንዴት እንደሚያወጡና እነደሚያሳድሱ ተጨማሪ መረጃ ሊሰጥዎ ይችላሉ።

አጠገብዎ ካለው ማንኛውም ፍርድ ቤት ጊዜያዊ ፕሮቴክሽን ኦርደር/የፍርድ ቤት መሳገጃ ሊያገኙ ይችላሉ ይህ ጊዜያዊ ማሳገጃ ለሁለት ሳምንት ብቻ ያገለግላል ከዛ በኋላ ፍርድ ቤት ተመልሰው በመሄድ ሙሉ ገደብ ለአንድ ዓመት ወይም ከዛ በላይ የሚያገለግል ሊሰጥዎ ይገባዎት ወይም አይገባዎት እንደሆነ ውሳኔ ያገኛሉ።

እንግሊዘኛ የመጀመሪያ ቋንቋዎ ካልሆነ ወይም እንግሊዘኛ መናገር የማይችል ሰው እየረዱ ከሆነ ገደብ ለማውጣት በሚቀጥለው አድራሻ እርዳታ ማግኘት ይችላሉ።

<u>ድህረ ገጽ/ውብ ሳይት - http://protectionorder.org/translations.htm</u>

**የእርስዎ ገንዘብ ነክ ጉዳይ**

የገንዘብ ችግር ከሚያጠቃዎት ሰው ለመራቅ/ለመለየት ከባድ ሊያደርግቦት ይችላል። ይህንን ሁኔታ ለመቋቋም ማለትም የገንዘብ፤ የምግብ ካርድ እና ለልጆችዎ ህክምና እርዳታ ለማግኘት <u>የማህበራዊ እና የጤና አገልግሎቶች ክፍልን ያነጋግሩ።</u>

የኢምግሬሽን ወይም የቤት ውስጥ ግጭት/ሁከት አድቮኬትዎ/ደጋፊዎች ለምን ዓይነት እርዳታ ብቁ እንደሆኑ ለማወቅ ይረዱዎታል።

- አንዳንድ ቋሚ ነዋሪነት ያላችው ስለባዎች/ተጠቂዎች ለበጎአድራጎት እና ለጤና አገልግሎቶች እንደ ገቢያችው መጠን ግልጋሎት ለማግኘት ብቃት ይኖራቸዋል
- ስደተኞች/ሪፊውጂዎች እዚህ አገር እንደገቡ ለመጀመሪያው ስምንት ወር ከበጎአድራጎትና ከጤና አገልግሎቶች እርዳታ ለመቀበል ብቁ ናችው ከዚያ በኋላ የኢምግራንትና የስደተኛ

ቤተሰቦች ለአስራ ስድስት ወራት ጊዜያዊ እርዳታ ለችግረኛ ቤተሰቦች/ታንፍ ለማግኘት ብቁ ናችው

- ቫዮለንስ አጌነስት ዊሜን አክት በኩል ለሕጋዊ ቋሚ ነዋሪነት አመልክተው ከሆነም ለቋሚ ነዋሪነት የሚሰጥ ግልጋሎት እርሶም ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ
- ሕጋዊ የመኖሪያ ፈቃድ ከሌሎት የአሜሪካን ነዋሪነት ያላቸው ልጆችዎ እንደሌላው ነዋሪ ሕዝብ ጠቀሜታ የአገልግሎቶች ጠቀሜታ ለመካፈል ይችላሉ።

ለተጨመማሪ መረጃ እና ለሕጋዊ ጉዳዮች እርዳታ ለማግኘት የዋሽንግተን ሕግ እርዳታን ይገናኙ በተለያዩ ቋንቋዎች መረጃ ይሰጣሉ።